# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 217066

ሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፊይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ መሰረት ሚዛኔ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ደስታ ብርቅነህ - ተወካይ ዳንኤል አዲስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 93008 በቀን 18/08/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 270731 በቀን 02/03/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በቀን 18/01/2013 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ወላጅ እናቴ ወ/ሮ አየለች ገበየሁ በአዲስ ከተማ ወረዳ 06 በቤት ቁጥር 132 ሲኖሩ ቆይተው ግንቦት 16/2012 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩና የሟች እናቴ ወራሽ መሆኔ በመ/ቁ 031941 የተረጋገጠ በመሆኑ የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ ድርሻዬ እንዲለይልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ ወደ ጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ባቀረቡት ክርክር የአመልካች ወላጅ እናት በሰራተኛነት አሁን የውርስ ሀብት በተባለው እና በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤ/ቁ 132 በሆነው ቤት ገብታ ቤቱን አለቅም በማለቷ በመ/ቁ 45137 ጉዳዩ ታይቶ በቀን 26/06/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካች ወላጅ እናት ቤቱን ለጣልቃ ገብ እንድትለቅ ተወስኗል፤ በመሆኑም የአመልካች ወላጅ እናትም ሆነ አመልካች መብት በሌላቸው ንብረት ላይ ውርስ እየተጣራ መሆኑ ታውቆ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ አመልካች በቤቱ ላይ ያላቸው መብት ፍ/ቤት በመ/ቁ 45137 በቀን 26/06/2007 ዓ.ም ከተሰጠው ውሳኔ ብቻ እንደሚመነጭ አመልካች ገልፀዋል፤ ፍ/ቤቱ ውሳኔውን አስቀርቦ እንደመረመረውም የአሁን ተጠሪ የቤ.ቁ 132 የሆነውን ቤት እንድትለቅላቸው የከሰሱበት ሲሆን የአመልካች እናት ወ/ሮ አየለች ገበየሁ በሌሉበት ጉዳዩ መታየቱን ውሳኔው ያሳያል ፤ በውሳኔው ሐተታም በዚህ ቤት ላይ ከሳሽ ወ/ሮ ደስታ ብርቅነህ የሟች አቶ ተክሌ ገብሬ ተተኪ ወራሽ በመሆናቸው በሪፖርቱ መሰረት የአቶ ተክሌን ግማሽ ድርሻ ሊወርሱ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በውሳኔው ክፍል ከሳሽ እና ተከሳሽ ቤቱን በጋራ እንዲካፈሉ በሚል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የውሳኔው ሀተታ እና ውሳኔው የሚጋጭ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም የአመልካች እናት በቤቱ ላይ ከህግም ሆነ ከኑዛዜ የሚመነጭ መብት ሳይኖራቸው ይህን ውሳኔ ብቻ ይዘው የቤቱ ግማሽ ድርሻ ይገባኛል ሊሉ አይችሉም፡፡ በሌላ በኩል በዚህ መዝገብ በተጣራው ሪፖርት እንኳ ይህ ቤት በአቶ ክፍሌ ገብሬ እና ወ/ሮ ብርቂ ወልደ ዩሐንስ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም የሚያስረዳው ቤቱን ወ/ሮ ብርቂ እና አቶ ተክሌ በጋራ ያፈሩት መሆኑን ሲሆን ግራ ቀኙን በመመርመር ለማወቅ እንደተቻለው ወ/ሮ ብርቂ ያለ ወራሽ የሞቱ በመሆኑ አመልካች የእርሳቸውን ድርሻ ይዘው እስካሁን እንደሚገኙ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ልወርስ ይገባኛል በማለት ያመለከቱት በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤ/ቁ 132 የሆነው ቤት የውርስ ሀብት ሆኖ ያልተገኘ በመሆኑ አመልካች በቤቱ ላይ ምንም አይነት መብት አይኖራቸውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙ ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 27/03/2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች እናት በፍ/ቤት ክርክር ተደርጎበት በተሰጠ ውሳኔ መብታቸው ተረጋግጦ እያለ የአመልካች አውራሽ ከህግም ሆነ ከኑዛዜ የመነጨ መብት የላቸውም ያለበት አግባብ ስህተት ነው፤ በስር ፍ/ቤት በመ/ቁ 45137 እናቴ ከተጠሪ ጋር በነበራት ክርክር ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ላይ ግማሽ መብት እንዳላት ተረጋግጦ የተወሰነና ውሳኔውም የጸና ነው፤ ተጠሪም በውሳኔው ተስማምተው በአፈጻጸም መ/ቁ 146048 ቤቱን እኩል ተካፍለው ጉዳያቸው በስምምነት ያለቀ መሆኑን ተጠሪ ራሳቸው ለፍ/ቤቱ በማቅረባቸው ስምምነቱ ተመዝግቦ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ተጠሪ ጣልቃ ለመግባት የጠየቁት የተፈጸመን ጉዳይ እንዳልተፈጸመ በማስመሰል ፍ/ቤትን በማታለል ሲሆን አሁን አመልካች በጠየቁት ንብረት ላይ ምንም አይነት መብት ሳይኖራቸው ወደ ክርክሩ እንዲገቡ መደረጉ የህግ ስህተት ነው፤ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ራሱን እንደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመቁጠር በአቻ ችሎት እና በአቻ ዳኛ የተሰጠውን ጸንቶ ያለ ውሳኔ የሚሽርበት አግባብም የለም፡፡ በመሆኑም ቀድሞ እናቴ በውሳኔ ያገኘችውን መብት በሚያሳጣ ሁኔታ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻርልኝ እና ውርሱ ተጣርቶ እንዲወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ቤት ግማሹ የአመልካች አውራሽ የሆኑት የሟች ወ/ሮ አየለች ገበየሁ ድርሻ መሆኑ በመ/ቁ 45137 ላይ ውሳኔ ያረፈበት መሆኑ ከመረጋገጡ አንጻር አመልካች መብት የላቸውም የመባሉን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 25/06/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ የአመልካች እናት ለክርክር ምክንያት በሆነው 2 ክፍል ቤት ላይ ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት ያላት ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ ማረጋገጥ ባለመቻሏ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ መደረጉ አግባብ ነው፤ አመልካች ባለመብት ሆንኩበት የምትለው መዝገብ ላይ እናቷ በመዝገቡ ላይ ቀርባ ካለመከራከሯም በላይ በውሳኔው ክፍል ላይ በአጻጻፍ ስህተት 1/2ኛ የቤቱን ክፍል እንድታስረክብ መጠቀሱ ዳኝነት ከፍላ መብቷን ለማስረከብ ክስ ባላቀረበችበት ሁኔታ የቤቱ ባለመብት የሚያደርጋት ካለመሆኑም በላይ የስር ፍ/ቤቶች አመልካችን ጠይቆ እንዳረጋገጠው የአመልካች እናት ቤቱን ተከሳሽ ሆና በቀረበችበት መዝገብ ላይ መብት ያገኘችበትን ህጋዊ መንገድ ማስረዳት ባለመቻሏ ምክንያት የተወሰነ አግባብ ያለው ውሳኔ ነው፤ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት አለኝ ብላ ልትከራከር የምትችልበት አግባብ ባለመኖሩ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ በማለት አቅርበዋል፡፡ አመልካችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንደመረመርነው የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረቡት ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ አየለች ገበየሁ በአዲስ ከተማ ወረዳ 06 በቤት ቁጥር 132 ሲኖሩ ቆይተው ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩና ወራሽ መሆኔ ስለተረጋገጠ የውርስ ሀብታቸው እንዲጣራ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ጣልቃ ገብተው የአመልካች ወላጅ እናት በሰራተኛነት በቤቱ ገብተው ቤቱን አለቅም በማለታቸው በመ/ቁ 45137 ጉዳዩ ታይቶ በቀን 26/06/2007 ዓ.ም ውሳኔ መሰጠቱን ጠቅሰው የአመልካች ወላጅ እናትም ሆነ አመልካች መብት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አስቀድሞ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 45137 የካቲት 26/2007 ዓ.ም የተሰጠውን ውሳኔ ተመልክቻለሁ በማለት በውሳኔው ሐተታ ላይ ከሳሽ ወ/ሮ ደስታ ብርቅነህ የሚች አቶ ተክሌ ገብሬ ተተኪ ወራሽ በመሆናቸው በሪፖርቱ መሰረት የአቶ ተክሌን ግማሽ ድርሻ ሊወርሱ እንደሚገባ ተመልክቷል፤ ነገር ግን በውሳኔው ክፍል ከሳሽ እና ተከሳሽ ቤቱን በጋራ እንዲካፈሉ በሚል ውሳኔ ተሰጥቷ፤ ይህም የሚያሳየው የውሳኔው ሀተታ እና ውሳኔው የሚጋጭ መሆኑን ነው በማለት አመልካች በቤቱ ላይ ምንም አይነት መብት አይኖራቸውም በማለት ወስኗል፡፡

እንደተመለከትነው በኮ/መ/ቁ 45137 ከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ ደስታ ብርቅነህ ተከሳሽ በነበሩት አየለች ገበየሁ ላይ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 132 በሆነው ላይ ክስ መስርተው ፍርድ ቤቱ በንብረቱ ላይ 1/2ኛ (ግማሽ) ድርሻ አላቸው በማለት ወስኖ ከሳሽና ተከሳሽ ከተቻለ በአይነት ካልተቻለ አንዱ ለአንዱ ግምት ከፍሎ ያስቀር ይህ ካልተቻለም በስምምነት ሸጠው ይካፈሉ ይህም ካልተቻለ በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል ይካፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይኸው ውሳኔ ያልተሸረና የፀና መሆኑ ያላከራከረ ሲሆን የተደረገው ክርክር እና የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔም ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡

እንደሚታወቀው በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም እስካልተደረገ ድረስ ውሳኔው ዋጋ ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 212 ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የውሳኔው ሀተታ እና ውሳኔው የሚጋጭ ነው በማለት በይግባኝ ታይቶ ያልተሸረን ውሳኔ ዋጋ በማሳጣት መወሰኑ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህን አለማረሙ የሚነቀፍ ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች ወ/ሮ ደስታ ብርቅነህ (የአሁን ተጠሪ) ቤቱን አስመልክቶ በወ/ሮ አየለች ገበየሁ (የአመልካች አውራሽ) ላይ ያቀረቡት ክስ አስቀድሞ በኮ/መ/ቁ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

45137 ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑና ይህ ውሳኔ ደረጃውን ጠብቆ ያልተለወጠ በመሆኑ አስገዳጅነት ያለው መሆኑ እየታወቀ አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው የህግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 93008 በቀን 18/08/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 270731 በቀን 02/03/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ቀሪውን ጉዳይ ተመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. የዕግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም